# ለኢትዮጵያ እና ለሕዝቦቿ ሲባል እንዲሁም ኢሕአዴግ ለራሱ ሲል ለሁለት የምርጫ ዘመናት በከፊልም ሆነ በሙሉ እራሱን ከስልጣን ያግል፡፡ ለምን? እንዴት?

<u>ኢትዮጵያን በብልሓት፡በማስተዋል እና በጥበብ እንታደጋት፡</u>
*ማሳሰቢያ፡ በእዚህ ፅሑፍ ላይ ነገሮችን በጉልህ ለማሳየት ጠንከር ያሉ ቃለቶችን ተጠቅሚያለሁ በቅድሚያ ይቅርታ፡፡ የፊደል ግድፈት ካለ አስተካክላችሁ አምብቡት፡፡ ይህ የግል አስተያዬቴ ነው፡፡ ያልጠራ አስተሳሰብ ካለ ጥይቁኝ፡፡ ለመወያየት መድረኩ ክፍት ነው፡፡*
*ከኢያሱ ኤፍሬም ለንደን የካቲት* 29/2010

1፡ *ብዙ ሰዎች አዋቂዎች ከትውልድ ትውልድ ተላልፎ የከተቧቸውን መፅሀፍት ያነባሉ ነገር ግን በውስጡ ያለውን ቁም ነገር ለምን እንዴት ፡ ከወዴት ለማ ከማ ብለው አይጠይቁም፡፡ ታሪካዊ አመጣጣቸውንም እና ሂደታቸውን በጥሞና አያገናዝቡም፡፡ ከታለስ* ( 624 – 546 *ቢሲ*) *እስከ ዘመናች ያለውን ፍልስፍና ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋራ አያዛመዱም፡፡ ለእዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆኑት በ* 50 *እና* 60*ዎች አመታት የተከሰቱት ወተት እና እቁላል እየቀለበ ኃይለስላሴ ያስተማራችው የተማሪ አብዮተኞች በተምሳሌነት የሚጠቀሱ የእናት ጡት ነካሽ ትውልዶች ናችው፡፡ ማርክስ እና ኢንግልስ ፡ ለእንግሊዝ ፡ለፈረሳይ እና ለጀርመን ችግር ብለው የፃፉትን ፍልስፍና፡ እንዲሁም ሌኒን እና ስታሊን ለራሺያ ችግር መፍቻ የከተቡትን መፅሐፍ እራቁታችን ለምንሔደው ኢትዮጵያኖች እና ከተወለዱበት ቅዬ ውጭ ለማቁት ህዝብ ላለበት ችግር መፍትሔ አድርገው በግድ እድንግተው አደረጉን፡፡ አሁንም ይግቱናል፡፡ በብሔር ብሔረሰቦች ሰም፡፡*
2፡ *በቅርቡ አንድ የለንደን ነዋሪ የአደዋን በአል አክብረን ከጨረስን በኋላ እረጅም የአውቶቢስ ጉዞ ባደረግንበት ወቅት ያጫወተኝ ከእዚህ ቀደም የያዝኩትን እምነት ይበልጥ አጠናከረልኝ፡፡ ይህ ወዳጄ እንዳለኝ በዛን ወቅት የነበርን በጣት የምንቆጠር ተማሪዎች አለኝ በግልብነት እና በጥራዝ ነጠቅነት ያነሳነው ጉዳይ እነሆ ዛሬ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል፡፡ ወለጋ ያለችን አዛውንቷን እናቴን እዳይገሉብኝ ነው ምፈራው አለኝ፡፡ ነገሩ እረጅም ነው የፅሁፌም አላማ ይህን ለማውጋት አይደለም፡፡ ከወዳጄ ጋራ ወደፊት በሰፊው እንደምናወጋበት እና የሚያቅውን ታሪክ ወደ መፀሐፍትነት እንዲቀይረው ተነጋግረን ተለያየን፡፡ ለሚቀጥለው ትውልድ ትምህርት ይሆናል እና በእዚህ ጉዳይ ላይ ወደፊት ተመልሼ እመጣበታለሁ፡፡ ለዛሬው ወደ ነጥቤ ልግባ፡፡*

3፡ *ብዙ ሰዎች በተለያየ መንገድ መፅሐፍ ቅዱስ ያነባሉ ፡፡ አልፈውም ጥቅስ እየተቀሱ ይሰብካሉ ያስተምራሉ፡፡ ነገር ግን ብዙዎቹ በውስጡ ያለውን ቁም ነገር የተረዱት አይመሰሉም፡፡ ይህም በመሆኑ ድርጊታችው እና አስተምህሮታቸው ለየ ቅል ነው፡፡ ሰለ መፅሀፍ ቅዱስ ሳነሳ ልሰብካችሁ፡ ወይም ላጠምቃችሁ አስቤ አይደለም ነገር ግን መፅሐፍ ቅዱስ ምን ያህል ፓለቲካዊ ማህበራዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ ትንታኔ እንደሚሰጥ ምን ያህሎቹ እንደምናውቅ ለመጠቆም ነው፡፡ በሚገርም ሁኔታ ከጥንታዊ የጋርዮሽ ስርነት* ( *አዳም እና ሔዋን*) *ጀምሮ እስከ ኮሚኒዝም ያስተማረ እያስተማረም ያለ መፅሀፍ ቅዱስ ነው፡፡ የመፅሀፍ ቅዱስ የአስተዳደርን ጥበብ፡ የጦርነትን ስልት፡ የፓለቲካን ጥበብ፡ እምነትን፡ ፅናትን ፡ፍቅርን፡ ምጣኔ ሀብትን፡ ፍትህን፡ መልካም አስተዳደርን እንክት አድርጎ ያስተምረናል፡፡እኛ ኢትዮጵያዊን ለ*2000 *አመታት በላይ ከእዚህ መፅሐፍ ጋራ ተቆራኝተን ኖረናል፡፡ ነገር ግን ሁላችንም ወፅሐፉን በቅጡ የተረዳነው አንመስልም፡፡ በተለይ መሪዎቻችን፡፡ ሲርቅ የጥንቶቹ ሲቀርብ የባለግዜዎቹ፡፡ ይህን ያልኩበት ምክንያት እኳን የምእራብዊያን ፍልስፍና ጠንቀው ልናውቅ ቀርተን ለ*2000 *ዘመናት የያዝነውን መፅሀፍ ጠንቅቀው አናውቀውም፡፡ ይህ እውነታ በተለይ ዛሬ መንግስት ሆነው የተቀመጠውን ኢሕአዴግ ይመለከታል፡ ላስረዳ ይፈቀድልኝ*

4፡ መልከ ጥፉ በስም ይደግፉ እንዲሉ፡፡ በምንም መልኩ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊ የሚል ጠረን የለለው ፡ ሕዝብን ጉሐፍ ብሎ የሚጠራ እራሱን ሕዝባዊ ብሎ ግን የሰየመ ፡፡ አብዮት ባልተዘራበት እራሱን አብዮታዊ አድርጎ ያበቀለ ፡ ለዲሚክራሲ ደቀመዝሙር ሳይሆን ይሁዳ ሆኖ ዲሞክራት የከዳ፡፡ በባል እና ሚስት ፡ በአባት እና ልጅ ፤ በወንድም እና በእህት፡በአጎትና በአክስት በቤተሰብ እየተመራ ግንባር ነኝ ብሎ ሐገር የሚመራ ድርጅት ቢኖር ይኸው የእኛው ጉድ ኢሕአዴግ ነው፡፡

5፡ በምእራፍ አራት ላይ የጠቀስኩትን መልእክት ከአንደኛ እስከ ሶስተኛ ምእራፍ ከጠቀሰኳቸው ነጥቦች ሲዛመድ ተራማጅ ነን ብለው የተነሱት ተማሪዎች ያነበቡትን ለም እንዴት ፡ ከወዴት ለማ ከማ የሚል ፍታሐዊ የሆነ የፍልስፍና ጥያቄ ሳያነሱ በጭፍን የዘላበዱ ቢኖሩ ከደርግ ጥይት የተረፉት አብዮተኛ ነኝ ባዮች የኢሕአዴግ አመራሮች እና በተቀዋሚው ጎራ የተሰለፉ መቃብር የረሳቸው የፓለቲካ አዛውቶች ናቸው፡፡ ልክ እንደ መፅሀፍ ቅዱሱ የሀሰት ሰባኪ ክርስቶስ ስለምን እንደተሰቀለ የማያወቁ ነገር ግን መሰቀሉን የሚሰብኩ የዘማናችን የሀሰት ፓስተሮች፡ የሀሰት ነብያቶች እና ጠማቂዎች አይነት መሆናችው ነው፡፡ ስለ ሐሰተኛ ነብያትን በተመለከተ ቅዱስ ቃሉ እንዲህ ይላል፡፡

6፡ የማቴዎስ ወንጌል 7፡ 15-29 እዲህ ይላል፡ [15] የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኵላዎች ከሆኑ ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።[16] ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን ከኵርንችትስ በለስ ይለቀማልን? [17] እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል።[18] መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም። [19] መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።

7፡ የማቴዎስ ወንጌል መልክት በሐይማኖት ውስጥ ላሉ ብቻ ሳይሆን የሚያገለግለው ዛሬ፡ በህዝብ ስም፡ የሚሰብኩ ነገር ግን በተግባር ፀረ-ህዝብ የሆኑ ፡ በዲሞክራሲ ስም የሚሰብኩ በተግባር ግን ፀረ-ዲሞክራሲ የሆኑ፡ ፡ በሀገር ስም የሚሰብኩ ነገር በተግባር ግን ፀረ-ሀገር የሆኑ ፡፡ በልማት ስም የሚሰብኩ በተግባር ግን ፀረ-ልማት የሆኑ ፡ በለውጥ (አብዮት) ስም ነገር ግን ተግባራችው ፀረ-ለውጥ (አብዮት) የሆኑትን የኢትዮጵያን ፓለቲከኞች ይመለከታል፡፡ ስለሆነም የማቴዎስ ወንጌል ፡፡ የማቴዎስ መልእክት ለኢትዮጵያ ፓለቲከኞች በሚል ቢተካ ይበልጥ ትርጉም ይሰጣል፡፡ በተለይ ለኢሕአዴግ፡፡

8፡ ኢሕአዲግ ወደ ስልጣን እንዲመጣ ከ100000 በላይ ህዝቦች ውድ እና አንድ ሕይወታችውን ገብረዋል፡፡ አምነውበት ይሁን ፡ተታለው፡ በጀሌነት ሆነ በጅልነት ገብተው ፡ በውዴታ ይሁን በግዴታ፡ ነቅተው ይሁን ደድበው ብቻ መለስን ወንበር ላይ ለማስቀመጥ ሺዎች ሞተዋል ፡ ሙት አይወቀስም እና በጦር አውድማ ላይ በፍልሚያ በተቃራኒ ወገን ሆነው ለወደቁት የኢትዮጵያዊን ልጆች ሁሉ ክብር እና ምስጋን ለእናተ ይሁን እላለሁ፡፡

9፡ ኢሕአዴግ ያነበበው ብቻ አይደለም ያልገባው እና ያልተረዳው ወይም የረሳው ፡፡ እንደ ክርስቶስም ደማችውን ያፈሰሱለትን በ100000 ሺዎቹ የሚቆጠሩት ህዝቦች ስለምን እንደሞቱ ሊገባው አልቻለም ወይም እረስቷቸዋል ማለት የቻላል ፡መለስንም ጨምሮ (ካከበሩት) ፡፡ ኢሕአዴግም እንደ ሀሰተኛው ጳጳስ እንደ ሀሰተኛው ፓስተሩ እንደ ሀሰተኛው ነብያት ስለ ክርሰቶስ መሰቀል ይሰብካል አንጂ የደሙ ዋጋ እና ትርጉሙ ምን እንደሆነ አልገባውም፡፡ ያ የተከፈለው ደም ለህዝቦች መብት ለሀገር ክብር መሆኑ ቀርቶ ለግለሰቦች ስልጣን እና ሀብት ማከማቻ ለሀገር ውርደት እና መከፋፈለ አደረጉት፡፡ እንዲያውም እንደ ሱሰኛ ሴይጣን አሁንም አሁንም ኢሕአዴግ ደም ይጠማዋል፡፡ በአለም ተደርጎ በማይታወቅ ሁኔታ የራሱን ወገን ግንባሩን እና ደረቱን በስናይፐር እየነደለ ይገለዋል፡፡ እዚህ ላይ ሊነገር በማይችል መንገድ ጠላት ያሉትን ያሶግዳሉ፡ ከነገሱ በኋላ የገበሩት ደም ወላድ በየቤቱ ትቁጠረው፡፡ የሀሰት ነቢያት እዳሉ ሁሉ የሀስት መሪዎችም አሉ፡፡

10፡ የሚያሳዝነው አሁንም አንዳድ የኢሕአዴግ አመራሮች አብዮት እያካሄድን ነው፡፡ አሁንም ለዲሞክራሲ እየታገልን ነው፡ አሁንም ለህዝብ እየታገልን ነው፡፡ አሁንም ሀገርን ለማበልፀግ እየሰራን ነው ብለው ያስባሉ በአደባባይ ይሰብካሉ፡፡ ይህ አስተሳሰብ ቅዠት ብቻ ሳየረሆን የአይምሮ መዣዠትን የሚሳይ ነው ፡፡ ጤናማ አይምሮ እዲህአያስብም ፡፡  ምክነያቱም እነሱም እንደሚያውቁት እኛም እንደምናውቀው እውነታው ከዛ የራቀ ነው እና ፡፡ ሀቁን አባቢዎቹም ሆኑ እራሱ ኢሕአዴግ ጠንቅቀው  ስለሚውቁት መድገም መደጋገም አምባቢን ማሰልቸት ነው፡፡ ይህ ውሸት ነው የሻቢያ እና የግብፅ ተላላኪዎች ናቸው እንዲህ ብለው የሚሉት ካላችሁ የራሳችሁን ቃለ ጉባዬ ተመልከቱት ከማለት ሌላ ምንም መልስ የኝም፡፡  አሁን ወደ ገደለው ልሂድ፡፡

## ለምን ኢሕአዴግ እራሱን ከስልጣን ማግለል አለበት፡

11፡ ኢትዮጵያ የኢሕአዴግ አይደለችም ለነገሩ የማንም የፓለቲካ ድርጅት ሀብት እና ንብረት አይደለችም ፡፡ ኢትዮጵያ የህዝቦቿ የኢትዮጵያን ነች፡፡ ይህን ሀቅ ያልተረዳ ፓለቲከኛ ወደ ፓለቲካ መድረኩ አይምጣ ከመጣም ሊመጣ የሚችለው በሽፍትነት ለነጠቃ ብቻ ነው፡፡
12፡ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያን ከሆነች እያዳንዱ ኢትዮጵያዊ በሀገሩ አስተዳደራዊ ጉዳይ ላይ እኩል መብት አለው፡፡ ይህን መቼም አብዮተኞቹ ያምናሉ፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ፓለቲከኞች ይህን ሀቅ ለይስሙላ ቢቀበሉትም በተግባር ግን የበግ ለምድ ለብሰው በበጎች መንጋ ውስጥ እያደቡ እንደ ሚገዋለሉ ተኩላ  ሆነው ነው የተገኙት ፡፡ አብዛኛው የፓለቲካ አቀንቃኝ የመጨረሻው ግቡ ስልጣን እና አብሮ ተያይዞ የሚገኘው ጥቅም ነው፡፡  ይህ በተለይ የተማሪ አብዪት የወለዳቸው ፓለቲከኞች ደዌ ነው፡፡ ለእዚህም ማሳያው በተለያየ ወቅት በሀገራችን ተከስተው የነበሩት የፓለቲካ ድርጅቶች ለምሳሌ ኢሕአፓ፡ መኢሶን፡ ቅንጅት፡ መድረክ የመሳሰሉትን አንጋፋ የፓለቲካ ድርጅቶች ያጠፋቸው ይህ የስልጣን ጥማታቸው እና ስካራቸው ነው፡፡ አሁንም ኢሕአዴግን ሊያጠፋው የደረሰው ካንሰር ይኸው ስልጣን እና ጥቅሙ ነው፡፡

13፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለዘመናት ሲቃ እና  መከራ አይተናል አሁንም እያየን ነው፡፡ ወደፊትም ላናይ የምንችልበት አንዳችም ምክንያት የለም በተለይ ለስልጣን ያለንን አስተሳሰብ ካልቀየርን፡፡ ኢትዮጵያ በተፈጥሮ ሐብታም ሀገር ነች  ግን በህዝቦቿ በተለይም እናስተዳድርሐለን ብለው በተነሱት መሪዎች ምክንያት የድሓ ድሓ ፡ የለማኝ ለማኝ፡ የውዳቂ ውዳቂ፡ የሆነች ሀገር ሆናለች፡፡ ይህ የማይቆረቁረው ፓለቲከኛ በስልጣን ሱስ  አይምሮው የናወዘ ግለሰብም ይሁን ቡድን የሚገኘው በእኛው መካከል ነው፡፡ ይህ በሽታ ነው፡ ይህ ካንሰር ነው፡ ይህ ደዌ ነው፡፡ ልናክመው ልናሶግደው ይገባል ፡፡ ስልጣናችን ለቀን አስፈላጊም ከሆነ ሕይወታችንን ሰውተን፡፡
14፡ ኢትዮጵያ በመጠፋፋት የፓለቲካ እሽክርክሪት መኖር የለባትም፡፡ ይህ የመጠፋፋት የፓለቲካ እሽክርክሪት በዘወርነው ቁጥር እንደ ኢትዮጵያዊነት እንዳንኖር የራሳችን መግደያ መርዝ እራሳችን እየቀመምን ነው፡፡ ጠላትም አያስፈልገንም፡፡ የመቀበሪያ ጉድጓዳችንን በጥልቀት እየቆፈርን ነው፡፡ ቆፋሪም አያስፈልገንም፡፡ ይህ እገለ ከእገሌ አይልም አራት ኪሎ ኖርክ ዳላስ፡ ለንደን ኖርክ ጅዳ  ሁላችሁም ከመጠየቅ ውጭ አትሆኑም፡፡ እስካሁን ያለው የኢትዮጵያ ፓለቲካ ሲታይ ሁለት አይነ ትጥፉ ከሀገር ጥፉ አይነት ዘይቤ አለው ይመስላል፡፡ ከፍ ሲልም፡ ግም ለግም አብረሽ አዝግም አይነት ነው ዘዬ ይይዛል፡፡ በእርግጥ ነው ኢትዮጵያ ፓለቲከኞች በአስተሳሰብ የገሙ የቀረኑ ናቸው፡፡ ይህነ ለማወቅ ታሪካችውን ማጥናት በቂ ነው፡፡  በእርግጥ ነው ድህነታችን ለእዚህ አንዱ ምክንያት ቢሆንም እንደ እዝርት የሚያዞረን እና የሚያሽከረክረን  ግን ደንቆሮነታችን ከአድማስ ባሻገር አርቀን ማየት አቅም ማጣታችን ፡ ከመርፌ ቀዳዳ የጠበበ አስተሳሰብ እና ስብእና መላበሳችን ነው፡፡ አነሰ ልጨምር?

15፡ ኢትዮጵያ በጠላት ተከባ ያለች ሀገር ነች፡ የኢትዮጵያ ግዛት ጠቦ ጠቦ አሁን ያለውን ቅርፅ የያዘው በጠላቶቿ ግፊት ነው፡፡ የነብዩን መሐመድ  ሕይወት ያዳነ ህዝብ ፡ ዛሬ ምድረ አረብ በጉሮራችን አጥንት ቀርቅሮ ያፋጀናል፡ ለኤርትራ መገንጠል  ጠንክሮ ያልሰራ የአረብ ሐገር የለም፡፡ ዛሬ ውኃ ከምናጠጣት ጅቡቲ ጀምሮ የውድቀታችን መንገድ የሚጠርጉልን ሀገሮች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ አባባም አሜሪካም ሆነ፡ እኅት ሩሲያ ( ውለታችውን ሳንረሳ)፡ወይም አክስት ቻይና

በየተራችው ኢ.ትዮጵያን አድምተዋል፡፡ ወደፊትም ያደሙናል፡፡ በነገራችን ላይ ኢሳያስን አስልጥና ያስጣጠቀች ሀገር ቻይና መሆኗን አንርሳ፡፡ ከዛም በፊት በቃኘው ጣቢያ ኢሳያስን ያሰለጠነችው አሜሪካ ነች ፡፡ እውነታው  እና ሀቁ ይህ በሆነበት ወቅት በተላያያ የታሪክ አጋጣሚ የፈጠርናትን ሀገር ይዘን በሰላም በፍቅር በመከባበር በልፅገን እንደመኖር  በዘር የተደራጁ ድርጅቶች  እያባሉን እርስ በእርሳችን እየተባለን እያናከሱት እዚህ ደርሰናል፡፡ ድሐ ሲጣላ እንጂ ሲፋቀር አያምርበትም የተባለ ይመስል፡፡

16፡ ወደፊት እንደ ሰው ለመኖር እና እንደ ሀገር ለመቀጠል ፡ የአለም መሳቂያ እና መሳለቂያ እንዳንሆን፡ ነገ ልጆቻችን የልጅ ጆቻችን ሀገር ኖሯቸው እንዲኖሩ ፡ በየ በርሐው እንደ ከብት ታርደው ብልታችው ኩላሊታችው በበዲዊን አረብ እንዳይቸበቸብ ከፈለግን 100 ሚሊዮናችንም አንዴ ቆም ብለን በአንድነት ልናስብ ይገባል ፡፡

17፡ ይህ ጉዳይ በግንባር ቀደምትነት የሚመለከተው ሀገር አስተዳድራለሁ ብሎ ሀገረ በጠመንጃ የተረከበው እና በጠመንጃ የሚያስተዳድረው፡ ጉሮሮ ላይ ቆሞ ግብር የሚያስከፍከው ስዩመ ጠመንጃው ኢ.ሕአዴግን ነው፡፡ ኢ.ሕአዴግ ሱባዬም ገብቶ ቢሆንም በጥልቀት ሊያስብበት ይገባል፡ ፡ ይህ ካላደረገ እና እኛም ያንን ካላደረግን ከሚመጣብን አርሚያዲጎን ልንቋቋመው ከቶ ልንተርፍ አንችልም፡፡

### ኢ.ሕአዴግ እና አማራጭ ሀይሎች ምን ማድረግ አለባቸው፡

18፡ ኢ.ሕአዴግ አሁን ማድረግ ያለበት አዲስ ምርጫ ማካሄድ ነው፡፡ ዲሞክራሲ ነው ምትሉት? አመትም ይፍጅ ሁለት አመት፡፡ በእዚህም ምርጫ ኢ.ሕአዴግ እንደ ኢ.ሕአዴግነቱ ሌሎችም ድርጅቶች ያለምንም አድሎ እና ኢ.ሕአዴግጋዊ ተንኮል እና ሻጥር ነፃ የሆነ ውድድር አድርገው ከህዝብ እንዳገኙት ድምፅ በተናጥልም ይሁን በጋራ መንግስት መመሰረት መቻል አለባቸው፡፡ በእዚህ ምርጫ ሂደት ውስጥ ኢ.ሕአዴግ ሶስት እድሎችን ይዞ የቀሰቅሳል ፡በመጀመሪያ ደረጃ ሙሉ በሙሉ ሊሸነፍ ይችልል፡ ሁለተኛ ነከፊል ሊያሸንፍ ይችላል፡ ሶስተኛ ሙሉ በሙሉ ሊያሸንፍ ይችላል፡፡ ይህ ሲሆን ኢ.ሕአዴግ እሰየው ሊል ይገባዋል፡፡ ይህ ነው እንግዲህ እውነተኛነት እና ሐቀኝነት፡ ይህ ነው ያነበቡትን በተግባር መተርጎም ማለት ይህ ነው የፈሰሰውን ደም ማክበር ማለት፡፡ ይህ ነው ከአድማስ ባሻገር ማየት መቻል ማለት፡፡ ይህ ነው በበሰለ በሰከነ አይምሮ ማሰብ ማለት፡፡ ይህ ነው ፅፈኝነትን መዋጋት ማለት፡፡ይህ ነው የኢ.ትዮጵያን ጠላቶች መዋጋት ማለት፡፡

19፡ ይህን ለማድረግ በቅድሚያ የተላያዩ የሚሰሩ እና ወደ አዲሱ  መንፈስ የሚያሻግሩ ዝግጅቶች መደረግ ይኖርባቸዋል የተለያዩ ደንቦች እና ህጎችም መውጣት ይገባቸዋል ፡ ለምሳሌ ኢ.ሕአዴግ ሌሎችን የፓለቲካ ድርጅቶች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንደ ሚቀበል ሁሉ ሌሎችም ድርጅቶች ኢ.ሕአዴግን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከነ ህገ መንግስቱ ሊቀበሉት ግድ ይላል፡፡ ያ ብቻ አይደለም በለስ ቀንቷችው ስልጣን ከያዙ እርስ በእርሳችው የበቀል እርምጃ እንዳይወሳሰዱ በህግ የፀና ውል ሊኖራችው ይገባል ፡፡ በኢ.ሕአዴግ አስተዳደር የተመሰረቱትን ፓለቲካዊ ፡ ኢ.ኮኖሚያዊ ማህበራዊ እና ወታደራዊ ተቋማትን ተቀብሎ መሄድ ግድ ይላል፡፡ እንደ የሁኔታው ማሻሻል እንጂ ማፍራረሱ አይጠቅመንም፡፡ ለምሳሌ ዛሬ ተነስተን ኤፈርትን እናፍርስ ማለት ድንቁርና ነው ባይሆን ህጋዊ እና ፍትሐዊ ወደሆነው አሰራር እንዲገባ ማድረግ እንጂ፡ በሌላው የኢ.ትዮጵያ የመረብ ደንነትን ተቋም ብናፈርስ ምንጎዳው እኛው ነን፡፡ ባይሆን የዜጎችን መብት ማፈኛ እንዳይሆን ህገ ደንብ የጣልበታል፡፡ ኢ.ሕአዴግ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ፡ ላጠፋው ጥፋት ምህረት ሊያገኝ ይገባል ፡፡ ይህ ነው የመጠፋፋት እሽክርክሪቱን ከመዘውር ሊያቆም የሚችለው እና ወደ ዲሞክራሲ ሊወስዳን የሚችለው መንገድ፡፡

20፡ ኢ.ሕአዴግ ሊገነዘብ የሚገባው ነገር ቢኖር እና በራሱም ከተማመነ ለስልጣን የሚያበቃው ድምፅ ባያገኝ እንኳን ከመቶ ያላነሱ ወንበሮችን ሊያገኝ የሚችልበት ሁኔታዎች መኖራቸውን ነው፡፡ ሌሎችም ቢሆኑ አሁን ባለው ሁኔታ አብላጫ ድምፅ አግኝተው እራሳቸውን ችለው መንግስት ለመመስረት አቅም ያለው ድርጅቶች የለም፡፡ ስለሆነም አማራጭ (ተቃዋሚ) ሀይሎች በጋራ የጥምር መንግስት ሊመሰርቱ ይችላሉ ፡ ወይም እራሱ ኢ.ሕአዴግ የጥምር መንግስት

ሊመሰርት የሚችልበት ሁኔታዎች ይፈጣራሉ ፡፡ በለስ ከቀናውም በራሱም መንግስት ሊመሰርት ይችላል፡፡ 50 +1 ካልን ማለት ነው፡፡ በእዚህ የፓለቲካ ሂደት ውስጥ የተለዩ የፓለቲካ አቋም ያላችው ቡድኖች ሊመጡ ይችላሉ፡፡ በኔ ግምት ግን 90 ከመቶ የራሱ ወጥ የሆነ የፓለቲካ ፍልስፍና ይዞ የሚበቅል ሳይሆን የአሜሪካ አለቅላቂ ነው፡፡ እዚህ ላይ መስራት እና መታገል ያለብን የአሜሪካንን ድስት ለማጠብ የምንዘጋጅ ፓለቲከኞች ሳንሆን የኢትዮጵያን የፓለቲካ ሰፌድ የምንሰፋ የእኛኑ ጥበብ የምንፈትል ፓለቲከኞች መሆን አለብን፡፡

21፡ ይህ ነው ኢትዮጵያን የማዳን ሂደት መሆን ያለበት፡፡ ከእዚህም በተጨማሪ አይምሯችንን እናስፋ ክፍት እናድርግ ካልን (መሰፋት ከቻለ) በብህሔር የሚደራጁ ድርጅቶች ለክልላችው እንጂ ለፌድራል መወዳደር እንደማይችሉ ስምምነት ላይ መደረስ አለበት፡፡ በተቻለ መጠን ብሔራዊ የሆኑ የፓለቲካ ድርጅቶች ለክልልም ሆነ የፌድራል መንግስት ለመመስረት ይወዳደራለሉ፡፡ ይህ በብሔር ስም ወደ ስልጣን ለመምጣት የሚደረገውን ትግል ያቆመዋል፡፡ ነሁደትም የብሔር ድርጅቶች ሀገራዊ እራይ እዲኖራችው ያደርጋችዋል፡፡ ይህ ነው ሀገር መገንባት ማለት ፡፡ይህ ነው ሀገር ማዳን ማለት፡፡ ይህ ነው እርቀ ማሰብ ማለት ፡ ይህ ነው ሀገርን በሻቢያ በግብፅ ሴራ እዳናውጥ እና ሊያድናት የሚስችለው የፓለቲካ ዘዴ እና መንገዱ፡፡የእውነት መንገድ አንድ ነች ሀሰተኞች አያልፉባትም፡፡

22፡ ኢሕአዴግ ሊረዳ እና ለያስብ የሚገባው ነጥብ በትንሹ በመቶዎቹ አመታት የምትኖር ሀገርን ነው፡፡ ይህ ከሆነ ለአንድ ወይም ለሁለት ስልጣን ዘመናት ( ለአምስት እና ለአስር አመታት) ከስልጣን ገለል ማለቱ ለኢሕአዴግ ይጠቅመዋል እንጂ አይጎዳውም፡፡ ከበሮ በሰው እጅ ያምር ሲይዙት ያደናግር ነው እና ኢሕአዴግን ሊተካው የሚችለው ቡድን የተጠበቀውን ውጤት ሊያመጣ የማይችልበት ብዙ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ከእዚህም ውስጥ ጎልቶ የሚጠቀሰው የንኡስ ከበርቴው ባህሪያቶች ናችው ፡፡ አበዛኞቹ የፓለቲካ ተዋኒያን ከንኡስ ከበርቴው የሚፈለቁ ናቸው፡፡ እነሱም በግለኝነት፡ በወላዋይነት፡ በዝርክርክነት፡ በአላማ ቢስነት፡ በችኩልነት፡ በአድር ባይነት እና በመሳሰሉት ተግደሮቶች የተሞሉ ናችው፡፡ ድንገት ውጤት ካመጡም እሰየው ነው ፡ ከነሱም መማር ነው፡፡ እዚህ ላይ ማየት ያለብን ሶስት ጉዳዮች አሉ፡፡ አንድ ዲሞክራሲ እስከ እፍጫው የተሰጠው ህዝብ ለእቃ እቃ ጨዋታ ግዜም አይኖረውም ፡ ሁለት ኢሕአዴግም ቢሆን ሌሎቹም በሙሉ ወይ በከፊል በተወዳዳሪነት የተቀመጡት ድርጅቶች እራሳችውን ማያ ፡ ማጠናከሪያ ግዜ ይኖራችዋል፡፡ ሶስተኛው እድሚያችው የገፋው አነጋፋ ፓለቲከኞች በአምስት እና በአስር አመታት ውስጥ ከመድረኩ በተለያየ መልኩ የመገለል እድል ይኖራአዋል ( ጡረታ የሚወጣው ጡረታ ይወጣል፡፡) ይህም ለተተኪው ትውልድ በር ከፋች ይሆናል፡፡ ተተኪውም ትውልድ ተወዳዳሪ በነበረበት ወቅት ፓለቲካን ተለማምዶ ተምሮ ወደ ስልጣን የመምጣት እድል ይኖረዋል፡፡ ትውልድ መገንባት ማለት ይህ ነው፡፡

23፡ በአዲሱ አወቃቀር የመናገር የመፃፍ መብቶች ያለ ገደብ የሚለቀቅበት ስርአት ይሆናል፡፡ ይህም ስለሆነ ነፃኒዲያዎች የሚመሰረተውን መንግስት ሰንን መያዝ የሚችል አቅም ይኖራችዋል ፡ መንግስት ከህዝብ እና ከሀገር ጥቅም ውጭ እንዳይሰራ መቆጣጠር ይቻላል ፡፡ ከህዝብ አይን እና ጆሮ የሚሰወር ነገር አይኖርም፡፡ ሕግ አውጪው ፡ ህግ ተርጓሚው እና ህግ አስፈፃሚ ስለሚለያዩ የአስተዳደር ጉድለትን፡ የዲሞክራሲ እና የሰባዊ ጥሰትን፡ ሙስናን በአንድ ጅምበር ማጥፋት እንችላለን፡፡ አንድ አባይ አይደለም አስር አባይን መገንባት አቅም ይኖረናል፡፡ ሰላም ባስ እንደ ስሙ በሰላም ከመቀሌ እስከ ሞያሌ በፍቅር ይጓዛል፡፡

24፡ ብዙ ሰዎች የሽግግር መንግስት እንዲቋቋም የሞፈልጉ የሚጠይቁ አሉ፡፡ ይህ ጥያቆ አግባብ እባ ተግባራዊ የሚሆንበት ወቅት እና ሰአት አለ፡፡ በኔ ግምት አሁን ለለብን ችግር መፍትሄ የሚያመጣም አይደለም ወቅቱም አይደለም፡፡ ይህ ጥያቄ እኔ ግምት ፓለቲካ ያልገባው ደነዝ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው ብዬ ነው የማስበው፡፡ ይህን ለማሳየት እና ስረግጦ ለማስረዳት ወዳ ቅርብ የታሪክ ታሪካችን ልውሰዳችሁ፡፡ደርግ ስልጣን በያዘ ማግስት እንደ አሁኖቹ የፓለቲካ አዋቂዎች በኢሕአፓ ጎራ የተሰለፉት በፓለቲካ እውቀት የመጠቅን እና የበቃን የሚሉ የዛሬው አዛውንቶች

የዛን ግዜ አፍላ ወጣት አብዮተኞች ድርግን ግዚያዊ ሕዝባዊ መንግስት ካላቋቋምክ ብለው ጎሮሮውን ያዙት፡፡ መያዝ ብቻ አይደለም ከአብዮት ጠባቂ እስከ መንግስቱ ድረስ የግድያ ሙከራ በማድረግ ጥያቂያችው መልስ እንዲያገኝ ሞከሩ፡፡ መንግስቱም የነብርን ጭራ አይዙም ከያዙም አይለቁም የሚለውን መርህ ተከትሎ አሜሪካ እና ወያኔ ተባብረው ሀራሬ እስኪገባ ድረስ ሺዎቹን እየጨረሰ እያሽጨረሰ ወንበሩ ላይ የተቀመጠው፡፡ ይህ ምን ያስተምረናል የመማር አቅሙ ካለን የሚያስተምረን ነገር ማንም የፓለቲካ ቡድን በቀላሉ ስልጣኑን ለቆ የሽግግር መንግስት አቋቁማለሁ እና ኑ ስልጣኔን ተረከቡ ወይም እንካፈል አይልም ተብሎም አያቅም፡፡ የሽግግር መንግስት በመሪዎችተቀባይ ቢሆን ኖሮ ወያኔ አምቦ ላይ ከመድረሶ በፊት መንግስቱ የሽግግር መንግስት ማቋቋም በቻለ ነበር፡ ጋዳፊ ተቀናቃኞቹ ቲሪፓሊ ከመግባታችው በፊት ይህን አማራች በወሰደ ነበር፡፡ ፓለቲከ በተለይ የያልሰለጠነ ፓለቲካ ያንን ህግ አይከተልም፡፡ ስልጣን ያውም በጠመንጃ የተከበበ እራስን ከአምላክ በታች ከሰው በላይ እድረጎ ስብአናን የመቅረፅ ሐያል አቅም አለመው፡፡  ለእዚህም ነው እንሽጋገር የሚለው ጥያቄ በንድፈ ሐሳብ ደረጃ የተሸሞነሞነ በተግባር ግን የደደበ የሚሆነው፡፡ መፍትሔው አንድና አንድ ነው፡፡ የተዋጣለትም ባይሆን በህዝብ ምርጫ መንግስት መመስረት ነው፡፡

## ሰውሩ አደጋ ፡ አትላንቲክን ያልተሻገረ ባርነት እና የእርስ በእርሱ እልቂት እንጠበቅ፡፡

25፡ በግሌ ኢሕአዴግ ይህን የሚያደርግ ልብ አለው ብዬ አላምንም ፡፡ ፈርኦን የቀይ ባህር ተክፍሎ እሰኪበላው ድረስ እስራኤሎችን አሳዷል፡፡ ኢሕአዲግን ከዘመናት በቀር የሚለየው ነገር አይታየኝም፡፡ ምክንያቱም ጥንታዊው (እንሰሳዊው) የፓለቲካ ህግ አሁንም ሕያው ነው እና፡፡ ከሞላ ጎደል ኢሕአዴግ የሚመራው በአራዊቶች ወይም በጫካ ህግጋት ነው፡፡ ከ27 አመታትም በኋላ ኢሕአዴግ እንደ ሰው ሊያስብ አልቻለም፡፡ ስለሆነም ዛሬም በጭንቅላቱ ሳይሆን በጠመጃው እያሰበ ነው፡፡ ስለሆነም ለችግራችን መፍትሔ  ጠመንጃ ነው ብሏል፡፡ እንዲያውም ይህን የመሰለ ሐሳብ ሲቀርብ የቂላቂል ሀሳብ ነው ብለው ሊሳለቁበት ይችላሉ፡፡ እኔ የምሰጠው መልስ ቂል ሆኜ ሀገሬን ህዝቤን ባድን እመርጣለሁ ብልጣብልጥ ሆኜ ሀገሬንም ወገኜንም በመጨረሻም እራሴን ከማጠፋ፡፡ ለስድስት ወር አይደለም ለአመታት ቢሆን አስቸኳይ ጊዜ ዐዋጅ  አይደለም የማርሻል ህግ ቢደነገግ ላለን ችግር መፍትሔ አያመጣም እንዲያውም ችግሩን ያባብሳል እንጂ፡፡
26፡ ኢሕአዴግ ስዩመ ጠማንጃ ነኝ ብሎ ስልጣኑን ሙጭጭ ካለ ቀኑ ይርዘም ይሆናል እንጂ መውደቁ አይቀርም፡፡ የዛን ግዜ አወዳደቁ አያምርም ሲወድቅም ሀገሪቱንም ይዞ አዘቅት ውስጥ ነው የሚገባው፡፡ በተለይ በአሜሪካኖች ግፊት ከወደቀ ( አሁን እየተሰራ ያለው ያንን ይመስላል) ተተኪው መንግስት ከኢሕአዴግ በባሰ መልኩ ፀረ-ኢትዮጵያ እና የአሜሪካ ጥቅም አስጠባቂ ሎሌ የሚሆን ይሆናል፡፡ በእዚህ በኩል ለራሱም ጥቅምም ቢሆን ኢሕአዴግ በብልጣ ብልጥነት የራሱን ልእልና በከፊል ከውጭ ሐይሎች የጠበቀ ድርጅት ነው እግረ መንገዱንም የኢትዮጵያን፡፡
27፡ ኢሕአዴግ በራሱ ችግር የራሱ እና የኢትዮጵያ ጠላት ቢሆንም በአሜሪካ የሚሰይመው ቡድን ከኢሕአዴግ የከፋ ሊሆን የሚችልበት ብዙ ፓለቲካዊ አና ኢኮኖሚያዊ እውነታዎች ይከሰታሉ፡፡ ምክንያቱም ስዩመ አሜሪካ ስለሚሆን የነጭ ቤት ሲጠራው አቤት ሲላክ ወዴት የሚል ይሆናል፡፡ በተላይ አሜሪካ የሰጠቸውን ማናችውንም የገንዘብ፡ የንግድ፡ የኢኮኖሚ ፓሊሲ አስፈፃሚ ይሆናል፡፡ሌላውን አይደለም የአባይን ግድብ የሚሸጥ መንግስት ሊኖረኝ ይችላል፡፡ ጨዋታው ነፃ ገበያ ነው እና፡፡  ይህም ስለሆነ በውጭ በተለይም ሙሉ በሙሉ የአሜሪካ መጫወቻ እንዳንሆን እራሳችን በራሳችን ፍቃድ እና ስምምነት የምናቋቁመው መንግስት ሊኖረን ይገባል ፡፤ተማክረው የፈሱት ፈስ እንደሚባለው ነው፡፡

28፡ የአሜሪካንን ጦስ ከሊቢያ እና ከኢራቅ መማር አለብን፡፡ ያ ሁሉ ጥፋት በሊቢያ ላይ ከተደረገ በኋላ እና ሊቢያን ወደ ባሪያ ፈንጋይነት ከቀየሩ በኋል፡፡ በሊቢያ ላይ ያደረግነው ስህተት ነው  አሉ አቦይ ኦባማ፡፡ በነገራችን ላይ ትላትና በእዩበሊዩ ቤተመንግስት ተገኝቶ አቦይ ኦባማ ኢሕአዲግን ዲሞክራተክ መንግስተ ነው ብሎ ያሞካሸ ወይ ያላገጠ የታላቋ የአሜሪካ በሪ ነው፡፡ ዛሬ ደግሞ ኤች-አር ሊሰጡን እየተዘጋጁ ነው፡፡ ለነገሩ ለኢሕአዴግ ሲንሰው ነው፡፡ ነጥቡን ያነሳሁት አሜሪካኖችን ተቃርኖ ለማሳየት ነው፡፡

29፡በነገራችን ላይ አሜሪካኖች ኢትዮጵያን የሚያቋት ከኮሪያ በፊት ነው፡የዛሬዋንም ደቡብ ኮሪያ አብረን ተባብረን ነው ያዳናት፡፡ ግን ዛሬ ኮሪያ የት ነች ያለችው እኛ የት ነን ያለነው፡፡ ገነት እና ሲኦል፡፡ በ50ዎቹ የነበረችውን ኮሪያ ለመመልከት ዩቲዩብ መግባት ትችላላችሁ፡፡ አሜሪካኖች በእርግጥ ለኛ አሳቢዎች ናቸውን? ሊሰመርበት የሚገባ ጥያቄ ነው፡፡ ትላንትናም ከእኛ ጋራ በነበሩበት ወቅት ከሁለተኛው አለም ጦርነት የተራረፉ መሳሪያዎች ጥለውልን ነበር ለዚያድ ባሬ አጋልጠውን የሄዱት፡፡ የንጉሱን ይሁን የደርጉን ግብአተ መሬቱ የተፈፀመው አሜሪካ ባደረገችው ፍትሐተ ፀሎት ነው፡፡ መለስም ይሁን ኢሳያስ  እጃችውን ይዛ ስልጣን ያስጨበጠችው ይችው አሜሪካ ነች፡፡ በነገራችን ላይ በመንግሱቱ ላይ የተደረገውን መፈንቀለ መንግስት የመራች ያስተባበረች እንዲከሽፍም ያደረገች እና ጀነራሎችም እንዲሰናበቱ ያደረገችው ይችው አሜሪካ ነች ብዬ እገምታለሁ፡፡ መንጋው ለመበተን እረኛውን አጥፋ ብሎ ያስተምራል  የፓለቲካው ሳይንስ፡፡ አሜሪካ ያደረገችው ያንን ነው፡፡ ለፍንጭ የሻለቃ ዳዊትን ቃለ መጠይቅ ልብ ብለው ይስሙ፡፡ ግን ገና ብዙ የሚጠና ሚስጢር አለው፡፡  አሜሪካንን እንደ አዳኝ መቁጠሩ እኛው በራሳችን ላይ በዲጂታል ዘመን ባነትን መቀበል ማለት ነው፡፡

30፡ ልላው አደጋ እንደ ሱማሌ በጎሳ ተከፋፍለን መተላለቅ ነው፡፡ በቅርቡ ከወደ ኦሮሚያ የተለቀቀ ተቀሳቃሽ ምስል እንደሚያሳየው አፉን በቅጡ ያልፋታ ልጅ ካራ ይዞ ወያኔን ነው ማርድበት ብሎ ሲናገር መስማት መጪው የሞት ድግስ ምን እንደሚመስል አመልካች  ነው፡፡ ኢሕአዴግ የክልል ፓሊስ እያለ ክልሎቹን አስታጥቋል፡፡ ከዛም አልፎ የመሳሪያው ገበያው በሐገሪቱ የደራ ነው፡፡ እራሱን ያስታጠቀ ብዙ ህዝብ አለ፡፡ ክፉ ቀን ከመጣ ወታደሩም ዘር ከሉጋም ይስባል፡ ደምም ከውኃ ይወፍራል ማለቱ አይቀርም፡፡ በተለያየ ወቅት በኢሕአዴግ ወታደሮች እና በክልል ታጣቂዎች መካከል የተከሰተው የቶክስ ልውውጥ፡፡የመልካም ልደት መግለጫ አይደለም፡፡ ሱማሌ በኦሮሞ ህዝብ ላይ በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲወስድ የተደረገው አሰነዋሪ ተግባር የነገውን አደጋ የሚሳይ ነው፡፡ የትግራይ አስተዳደር በማን አለበኝነት ከአማራ ቆርሶ የወስደው መሬት ካልተመለሰ ትላንትም ደም አስከፈሏ ዛሬም ደም ያስከፈላል ወደፊትም ደም የሚያስከፍል ነው፡፡ይዋል ይደር እንጂ ጎንደር የወለደቻችው የእስራኤል ልጆች ወልቃይት መምጣታቸው የማይቀር ነው፡፡ እነ አቦይ ምን እንደነካችው ባለውቅም መርዙን በጥብጠው በጥብጠው አስቀመጠውታል፡፤ የእዚህ መርዝ አርካሹ፡፡ መርዙን የቀመመው አካል ነው ፡፡ ካረከስ በራስም መርዝ መጥፋት ስለሚኖር  ሊታሰብበት ይገባል፡፡

31፡ እንግዲህ ናይ አቦይ ኢሕአዴግ ሆይ የአቅማችን ያህል መክረንሀል ፡፡ ሰው ያለውን ከሰጠ ንፉግ አይባልም ፡፡ድሮም እንደ መከርን እንደ ሰጠን ነው ፡፡ የሀገር ፍቅር ግድ ስለሚል ይህን ብያለሁ ፡፡ ከጎደለ ሙሉበት ከተሳሳተ አርሙት፡፡ ግን አሁንም እንደ ትላንትናው መስሚያዬ ኮብል ነው የምትሉ ከሆነ እና የፈርኦንን ልብ አምላከ ጠመንጃ ከሰጣችሁ  ከሰማይ ሳይሆነ ከምድር መቅሰፍቶች ይመጡባቹሀል ፡፡ እየተከሰቱም ነው  የተቀረው የቡክር ልጅን መንጠቁ ላይ ነው እሱም ብቅ ብቅ ማለት ጀምሯል፡፡ ለብሔረ ኢሕአዴግ የሚከፈት የሚዘጋ ቀይ ባህር አይኖርም በምትኩ የጥፋትም ውኃ ይዘንባል ይሆናል እንጂ፡  የጥፋት ውኃ በዘነበበ ወቅት በመርከቧ ላይ ሚሳፈሩት በጣም ጥቂቶች ብቻ ይሆናሉ፡፡ እኔ በኩል ታኳዬን አሰርቻለሁ፡፡

## ማሳረጊያ

32፡ እንደ ሰው እንደ ሀገር መኖር እና መቀጠል ካሰብን በጋራ ተባብረን ማደግ መበልፀግ ከተመኘን፡ የያዝነውን የህዳሴ ጉዞ ከግብ ለማድረስ ከፈለግን፡፡ በጋራ የሚያስማማን ነገር መፍጠር መቻል አለብን፡፡የማኪቬሊን ፓለቲካ መተው አለብን፡፡ ሁሉም በሀገሩ የመብት ባለቤት ሊሆን ይገባል በሐሰብም ባንስማማም፡፡የብሔር እኩልነት ለመጠፋፋት ምክንያት መሆን የለበትም፡፡ የድንቁርና መንገዳችን በእውቀት ብርሐን መተካት መመራት አለበት፡፡በብሔር መደራጀቱ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ብሔራዊ መንግስታችንን ግን ብሔራዊ በሆኑ የፓለቲካ አደረጃጀት ማዋቀየር አለብን፡፡ ሠራዊቱ የሞያ ግዴታውን ይወጣ የፓለቲካ ድርጅቶች ዱላ መሆኑ ይቁም፡፡በጋራ ሀብት የምናፈራበት ስርአት እንመስርት፡፡ ለምሳሌ ሰላም ባስ የኢትዮጵያ

ባስ ይሁን፡፡ ከድንበራችን ውጪ ያሉትን ግዚያዊ እና ቋሚ ጠላት እና ወዳጅ ለይተን እንወቅ ፡ ጣሊያን ሲመጣ ለጣሊን ማደር፡ አሜሪካ ሲመጣ ለአሜሪካ ማደር፡ ሩሲያ ሲመጣ ለሩሲያ ማደር፡ ቻይና ሲመጣ ለቻይና ማደር አረብ ሲመጣ ለአረብ ማደር እናቁም፡፡ የማንማ ፍርፋሪ ለቃሚ እና ድስትአለቅላቂ አንሁን፡፡ የራሳችን ፍልስፍና ይኑረን፡፡ በአካልም በአይምሮም ባሪያ አንሁን፡ ለእዚህ መንገዱ አንድና አንድ ብቻ ነው በህዝብ የተመረጠ መንግስት በህዝብ የተወደደ ምንግስት መመስረተ ነው፡፡ ያ ካልሆን ግን ገላችን እንደ መኪና መለዋወጫ በአለም ገበያ ይቸበቸባል፡፡ ያለ ክብር መሰድ ለስራም ወደ አረብ እና ወደ ተለያዬ ሀገራት መሄድ ከላይ ከጠቀስኩት ክስተት ብዙም አይለይም፡፡ እንደ ከብት በየ በረሐው አንታረድ፡፡

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
March 11, 2018